COMMONWEALTH of VIRGINIA
(ኮመንዌልዝ ኦፍ ቨርጂኒያ)
Department of Social Services (የማህበራዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት)
የኮሚሽነሩ ጽ / ቤት

S. Duke Storen
ኮሚሽነር

ኦገስት 7, 2026

ውድ የ ቨርጂኒያ የቸርቻሮ ነጋዴዎች፣

በሺዎች ለሚቆጠሩ የቨርጂኒያ ቤተሰቦች፣ SNAP የምግብ ወጪን በመሸፈን እና ጤናማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የወደፊት ህይወት እንዲኖራቸው በማድረግ ድጋፍ ይሰጣል። የቸርቻሮ ነጋዴዎችም የዚህ ተልእኮ አስፈላጊ አካል ናቸው፣ እና በ Virginia's SNAP አስፈላጊ የተባለ ለውጥ ተግባራዊ ስናደርግ፣ እናንተ ለምታሳዩን ቀጣይነት ያለው አጋርነት አድናቆታችን የላቀ ነው።

ከ ህዳር 1፣ 2026 ጀምሮ፣ የ SNAP ጥቅማጥቅሞች **ተጨማሪ ስኳር ወይም አርቲፊሻል ማጣፈጫ ያላቸው ካርቦኔትድ መጠጦችን**(ሶዳ፣ ዳይት/ዜሮ ሶዳ እና ካርቦኔትድ ኃይል ሰጪ መዐጠጦችን ጨምሮ) ለመግዛት ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም። ሁሉም ሌሎች መጠጦች ለ SNAP ብቁ ሆነው ይቆያሉ።

ይህ ለውጥ **የአንላይን ግብይቶችን ጨምሮ በ ቨርጂኒያ ውስጥ ባሉ ሁሉም የSNAP ግብይቶች** ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ቨርጂኒያ ይህን ማሻሻያ በጸደቀው የአሜሪካ ግብርና ዲፓርትመንት (USDA) የልዩ ፈቃድ መሠረት ተግባራዊ እያደረገች ነው። (ስለዚህ ልዩ ፈቃድ ተጨማሪ መረጃ www.fns.usda.gov/snap/waivers/foodrestriction/virginia) ላይ ይገኛል።

ለዚህ ማሻሻያ ለመዘጋጀት፡

- **የሽያጭ ነጥብ ስርዓትዎ (pointofsale system)** ህዳር 1 ጀምሮ እነዚህን የተከለከሉ ካርቦኔትድ እና ማጣፈጫ ያለባቸው መጠጦችን እንዲያግድ ማድረጉን።
- በ SNAP ብቁነት ለውጦች ላይ ያተኮረ ስልጠና ለሰራተኞችዎ ይስጡ።

የስርዓት ማሻሻያዎችን ለመደገፍ፣ በዚህ ለውጥ የሚነኩ **ምርቶችን ሁለንተናዊ የምርት ኮድ (Universal Product Code (UPC))** ዝርዝር እናቀርባለን። በቅርቡ ከእኛ ይህን ዝርዝር የያዘ የተለየ ኢሜይል እንዲደርስዎ መጠበቅ ይችላሉ።

የቨርጂኒያ የማህበራዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት (Virginia Department of Social Services (VDSS)) እርስዎን እና ንግድዎን ለመደገፍ ዝግጁ መሆኑን ላረጋግጥልዎ እፈልጋለሁ።

የሚከተሉትን ማቅረባችንን እንቀጥላለን -

- የተከለከሉ ዕቃዎች የተመለከቱ ግልጽ መስፈርቶች
- የማስታወቂያ ምልክት አብነቶች እና ለደንበኞች የሚቀርቡ መረጃዎች
- በኢሜይል የሚሰጥ የቴክኒክ ድጋፍ
- አማራጭ ቄቢናሮች፣
- ጥያቄዎችን የመጠየቅ ዕድል ለእርስዎ

የቨርጂንያ ቸርቻሪዎች
ኦገስት 7, 2026
ግጽ ሁለት


ለደንበኞች የሚቀርቡ የመረጃ ምንጮች፣ ብቁ እና ብቁ ያልሆኑ መጠጦች የተመለከቱ ግልጽ ዝርዝሮች፣ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና ተጨማሪ መረጃ **www.dss.virginia.gov/SNAPHealthy** ላይ ይገኛሉ።

ጥያቄዎች?
ሁሉም የ SNAP የተፈቀደላቸው ቸርቻሪዎች ስለ SNAP Healthy እና እንዲሁም ወደ ቺፕ/EMV ካርዶች ሽግግር የተመለከተ ለ አንድ ሰዓት የሚቆይ ዌቢናራችን ላይ ከኤጀንሲያችን ጋር እንዲቀላቀሉ ተጋብዘዋል። የVDSS መሪዎች ከቸርቻሮ ነጋዴዎች መረጃ ያቀርባሉ እንደዚሁም ከቸርቻሪዎች የሚመጡ ጥያቄዎችን ያስተናግዳሉ።
እባክዎን ከሁለቱም አማራጮች አንዱ ላይ ይቀላቀሉን፡

- ሐሙስ፣ ኦገስት 20, 2026, 2 - 3 p.m. – ለመመዝገብ እዚህ ላይ ይጫኑ
- ሐሙስ፣ ሴፕቴምበር 3, 2026, 2 - 3 p.m. – ለመመዝገብ እዚህ ላይ ይጫኑ

ከደንበኞች እና ከሰራተኞች ጋር ሂደቱ በቀላሉ እንዲከናወን ድጋፍ በመስጠት ለምታደርጉት ትብብር እናመሰግናለን።

ከ ሰላምታ ጋር



S. Duke Storen